# ለጋራ ርስታችን ኢትዮጵያ ምን እናድርግ?

ይህንን አስተያየት ለመጫጫር የምሞክር ኢትዮጵያዊ ዛሬ በሕይወት በእርግና ከሚገኙት ትውልድ አባል አይደለሁም። የ ‹‹ያ›› የሚባለው ወይም ‹‹ተራራ አንቀጠቀጥኩ›› የሚለው ትውልድም አባል አይደለሁም። የ‹አሁኑ› ትውልድ አባል ነኝ ለማለትም እቸገራለሁ። በ50ዎቹ ማብቂያ በ60ው ዋዜማ ላይ የተገኘሁ በመሆኔ። የእኔ ትውልድ የኖረበትንና ያለበትን ሁኔታ ከዚህ በመቀጠል የምዘረዝራቸው እውነታዎች የሚገልጹት ይመስለኛል። ከልደት ጀምሮ አሁን እስካለንበት ሰዓት ድረስ አንድ በጎ ቀን ያላየ ትውልድ፤ አገዛዞች ሕዝባችንንና አገራችንን በእጃቸው ጭብጥ በእግራቸው እርግጥ አድርገው፣ እንደ ሰም አቅልጠው እንደ ገል ቀጥቅጠው በመግዛት እንደ ልባቸው የሚፈነጩባት ኢትዮጵያ፤ አገዛዞች በጉልበት በተቀየሩ ቁጥር ከምንም እንደትጀምር የተፈረደባት ኢትዮጵያ፤ አሳዳሪዎቻቸው ባዕዳን የሆኑ እና ለነዚሁ በቅጠረኝነት/በባንዳነት የሚያገለግሉ አገዛዞች የሠለጠኑባት ኢትዮጵያ፤ ነፃነት፣ ፈቃደ ሕዝብ ያለበት አስተዳደር እና ሰላም የራቁባት ኢትዮጵያ፤ በዚህም ምክንያት የማያባራ ሰቈቃ ፣ ጦርነት፣ ችጋር፣ ረሃብ፣ ድንቁርና፣ ድህነት የሰፈነባት ኢትዮጵያ፤ ምሁራን በአስደንጋጭ ዝምታ ወይም በሆድ አደርነት የሚገኙባት ኢትዮጵያ፤ መካሪ ገሣጭ የሃይማኖት አባትና የአገር ሽማግሌ የታጣባት ኢትዮጵያ፤ መልካም ማኅበራዊ እሴቶቻችን ተመናምነው ማኅበራዊ ድቀት የነገሠባት ኢትዮጵያ፤ ከአገር በቀሉም ሆነ ከዘመናዊው ትምህርትና እውቀት ሳይሆን ከሁለት ያጣ የሆነውና በድቡሽት ላይ የተመሠረተው ትውልድ የሚተራመስባት ኢትዮጵያ፤ ለሕዝብ ቆመናል በሚሉ የፖለቲካ፣ የሲቪል፣ ወይም ሌሎች ማኅበራት አባላትና መሪዎች መደማመጥ በጭራሽ የጠፋባት ኢትዮጵያ፤ በነዚህ ሁሉ ማዕበላት ሲናጥ የቆየውና እየተናጠ ያለ ትውልድ የሚገኝባት ኢትዮጵያ። አለመታደል ሆኖ የተዘረዘሩት ሁሉ በመጥፎ ውርስነት ለአሁኑም ትውልድ የተላለፉ የዚህም ትውልድ መገለጫዎች ናቸው።

ይህ ለምን ሆነ? ምክንያትና ሰበቦቹ ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ምክንያት ግን ለሁላችን አባት አዳምም አላዋጣውም። ከፀጋ ከመራቆት፣ እግዚአብሔርን ያህል ጌታ ገነትን ያህል ቦታ ከማጣት አላዳነውም። ንስሓና በጎ ሥራ፣ ከሁሉም በላይ የአምላኩ ቤዛነት ነው ድኅነትን ያስገኘለት፣ ወደ ቀደመ ክብሩ የመለሰው። የኛስ ንስሓ ምን ይሆን? የሚጠበቅብንስ በጎ ሥራ? የሚታደገን/ቤዛ የሚሆነንስ ማነው?

ምንም የማያወቁ ሕፃናት እና (እነሱ ተሰቃይተው/ሞተው ለእኛ ሕይወት የሰጡን) እናቶቻችን በምን እዳቸው ነው ርህራሄ በሌላቸው፣ ከዚህች የጋራ ርስታችን ከምንላት በበቀሉ እንክርዳድ ‹አውሬዎች› በአደባባይ ሲገደሉ ‹ከዚህ የባሰ አታምጣ›፣ ‹እሱ እንደ ፈረደብን› እያልን የምንዘምርና ምንም እንዳልሆነ ቆጥረን ‹የዕለት ተዕለት ኑሮአችንን› የምንቀጥል? ለግፍና በደሉ፣ እሪታና ዋይታው መቀጠል ተጠያቂዎች እኛው

ኢትዮጵያውያን ነን። ታላቁና አንጋፋው የአገራችን ምሁር ደጋግመው እንደተናገሩት እኛ ኢትዮጵያውያን ጫንቃችንን አመቻችተን ግፍና በደል ለመሸከም ዝግጁ በመሆናችን ነው፤ በስንፍናችን የሚጠበቅብንን ባለማድረጋችንም ሆነ የማይጠበቅብንን በማድረጋችን ነው፤ ለአስደንጋጭ ዝምታችንም ሆነ ለድርጊታችን እንደ ሕፃናት ኃላፊነት ለመውሰድ ዝግጁ አለመሆናችን ነው፤እግዚአብሔር የግፍና ዓመፃ ሁሉ ተባባሪ ይመስል ባርኮ የሰጠንን ርስታችን ኢትዮጵያን አርመን፣ ኮትኩተን፣ ተከባክበን ሠላሳ፣ ስድሳና መቶ ንጹሕ ‹ስንዴዎችን› የምታፈራ መልካም እርሻ ማድረግ ስንችል እያወቅንና በቸልተኝነት እርሻው እንክርዳዶችን ሲያፈራ፣ እሾህና አሜከላ ሲበቀልበት እንዴት እግዚአብሔር ተጠያቂ ሊሆን ይችላል? ኧረ ወገን ይብቃን። ከሰብአዊነት ደረጃ ወርዶ ዘቅጦ መኖር አላንገሸገሸንም ማለት ነው? የአገር ጭራ መሆን አያንገበግበንም? የቀደሙ የሃይማኖት አባቶች ሲያስተምሩ በጽሑፍም እንዳቆዩልን እግዚአብሔር ጽድቅን አይደለም ኃጢአትን እንኳ የሚያስፈጽም አምላክ ነው ይላሉ። የኃጢአት ተባባሪ ሆኖ ነው እንዲህ ያሉት? በጭራሽ! እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ባለ አእምሮ አድርጎ ፈጥሮታል። የሚመለከውም በነፃነት ነው። ይህን ነፃነቱንና ክፉውን ከበጎ የሚለይበትን አእምሮ ተጠቅሞ የፈቀደውን ማድረግ የሰው ልጅ ምርጫ ነው። ይህንንም ፈቃድ፣ ምርጫ ሲከተል የሚያስከትለውንም ውጤት ለመቀበል ተዘጋጅቷል ማለት ነው። እንደ ማር የጣፈጠችውንና የወደዳትን ኃጢአት እንደ እሬት መሮትና አንገሽግሾት እንዲተወው ዕድል ይሰጠዋል። አልመለስም አሻፈረኝ ካለ ግን የኃጢአትን ደመወዝ ይቀበላል። እኛም ለድርጊታችንም ሆነ ለዝምታችን ኃላፊነት ወስደን ግፍ፣ጭቆና፣ በደል፣ ባጠቃላይ ባርነት አንገሽግሾናል ብለን በተግባር የሚተረጐም ቁርጥ ኅሊና ሲኖረን የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርም ፈቃዳችንን ይፈጽምልናል፤ የምንፈልጋቸው ነፃነት፣ እኩልነት እና የሕዝብ ፈቃድ ያለበት አስተዳደር እውን ይሆናሉ።

በእኔ እምነት አሁን ያለው የወያኔ አገዛዝ የሚጠገንበት/የሚሻሻልበት ዕድል የለውም። ይህንን ማሰብ ጉም መዝገን ወይም ነፋስን መጐሰም ነው የሚመስለኝ። በርካታ ዕድሎችን አምክነውና አጨናግፈው ቁናቸው የተሠፈረ፣ ጽዋቸው የሞላ ይመስለኛል። ወያኔና ተላላኪ አሽከሮቹ የቀራቸው የዘሩትን ማጨድ ብቻ ይመስለኛል። ተደጋግሞ እንደተነገረው ይህ በምኞች ብቻ አይመጣም። እያንዳንዳችን ከከፍተኛ ጥንቃቄና ኃላፊነት ጋር የሚጠበቁብን ተግባራት አሉን። እነዚህ ተግባራት የሚከተሉትን አንኳር አስተሳሰቦች ታሳቢ ያደርጋሉ።

፩ኛ/ የወያኔ አገዛዝ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ጠላትና ሕዝቡም የዚህ አስከፊ ሥርዓት ገፈት ቀማሽ መሆኑ፤

፪ኛ/ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ማናቸውም ችግሮች፣ ተግዳሮቶች፣አለመግባባቶች የሚፈቱት ለሁሉም ኢትዮጵያዊ (ፆታ፣ ጎሣ፣ ሃይማኖት ወ.ዘ.ተ ሳይለይ) እኩል የሆነች በሕዝብ

ፈቃድ ላይ የተመሠረተች፣ ነፃነት፣ እኩልነት፣ ፍትሕና የሕግ የበላይነት የሚሰፍንባት ኢትዮጵያን በመመሥረት መሆኑ፤

፫ኛ/ አገዛዙ እስኪወገድ ድረስ ማናቸውም ልዩነቶቻችን ለጊዜው ታግሰን በማቆየት በጋራ በምንመሠርተው አዲስ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ሂደት ዐበይት ቅሬታዎችችን ሁሉ ተነቅሰው ወጥተው በሰለጠነ መንገድ፣ በእኩልነትና በመደማመጥ ዘላቂ መፍትሄ ማበጀትን፤

ስለዚህ ምን እናድርግ? ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ድርሻ አለው።

ሀ/ ከምሁራኑ (በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምትገኙ)

ታዋቂው ጥቁር አሜሪካዊ የሰብአዊ መብት ተሟጋች መሪ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር በአንድ ወቅት እንዲህ ሲል ተናገሯል። “We will have to repent in this generation not merely for the hateful words and actions of the bad people but for the appalling silence of the good people.” በግርድፉ ወደ አማርኛ ሲመለስ መልእክቱ ይህን ይመስላል፤ ***በዚህ ትውልድ የምንጸጸተው እንዲያው ስለ እኩይ ሰዎች የጥላቻ ቃላትና ድርጊት ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም ስለ መልካም ሰዎች አስደንጋጭ ዝምታ እንጂ።***

በዚህ ሳይማር ባስተማራችሁ ሕዝብ መካከል የብርሃን ቀንዲል/ የምታበሩ አዕናቍ ለመሆን ካሰባችሁ፣ እውነትን ብቻ ለመናገር የተዘጋጃችሁ ከሆናችሁ፣ የሕዝባችሁ የዘመናት ሰቈቃ ከልባችሁ ጠልቆ የሚሰማችሁና ይህች የጋራ ርስታችን ኢትዮጵያ በወያኔ አገዛዝ የደረሰባት በታሪኳ ታይቶ የማይታወቀ መዋረድ የሚቆጠቁጣችሁ ምሁራን ካላችሁ፣ ለሁላችን ግራ ያጋባ ዝምታችሁ በዚህ የምጥ ወቅት ካልተሰበረ እስከ መቼ ነው የሚቀጥለው? ነፃነትና ሰላም፣ ፍትሕና እኩልነት ለተጠማ፣ ሰብአዊ ክብሩ ተጠብቆለት ለመኖር በእጅጉ ለሚናፍቅ ወገናችሁ በእውነት የምትጨነቁና የምታስቡ ከሆነ እጅግ ዘግይቷል ከሚባል በቀር ጊዜው አሁን ነው። በወያኔ የጎሣ ወጥመድና ልዩ ልዩ የመከፋፈያ ተንኮሎች ሳትተበተቡ የፖለቲካና የሲቪክ ማኅበራትን፣ ተማሪዎችን በአጠቃላይ ሕዝባችሁ ለአንድ ዓላማ እንዲሰባሰቡ ፈር አስይዟቸው፤ ዘላቂውን አሻግረው እንዲያዩ በጥበብና በአስተዋይነት ምሩአቸው፤ ግጭቶች እንዳይከሠቱ ምከሯቸው፤ ከተከሠቱም ሳይቃጠል በቅጠል ብላችሁ አደጋ ሳያስከትሉ የሚፈቱበትን አማራጮች አሳዩአቸው። ሕዝባዊ እምቢተኝነትን ተከታታይነት ባለው መልኩ ለሕዝባችሁ አስተምሩ አሳውቁ። ሳታፍሩና ሳትፈሩ ስለ እውነት መስክሩ ነፃ የሚያወጣችሁ እውነት ብቻ ነውና።

ለ/ የፖለቲካ ማኅበራት/ድርጅቶች (በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምትገኙ)

የታሪክ አራሙቻ የሆነውን የወያኔ አገዛዝ ለማስወገድ ሁኔታዎች ሁሉ አመቺ ይመስላሉ፡፡ ሂደቱን ለማፋጠን ከሁሉም በላይ ሕዝብን እንወክላለን አርነት እናወጣለን በማለት ከተደራጁ የፖለቲካ ማኅበራት የሚጠበቀው ‹‹ዓመልን በጉያ አድርጎ›› በቅድሚያ ወያኔን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ለማውረድ ስልታዊ ኅብረት/አንድነት መፍጠር ነው፡፡ ለወያኔ አንገዛም በቃን እምቢኝ አሻፈረኝ እያሉ በአራቱም ማዕዘናት ውድ ሕይወታቸውን የሚሰጡ የኢትዮጵያ ልጆች ትግላቸውን የሚያቀናጅ የሚያስተባብር አጥተዋል፡፡ የወያኔ የከፋፈልህ ግዛ ሰለባ ሆናችሁ ወይም በሌላ ምክንያት በጎሣ የተደራጃችሁ ወይም ዜግነትን መሠረት አድርጋችሁ የተደራጃችሁ የፖለቲካ ማኅበራት እውነት ዓላማችሁ ከሥልጣን በዘለለ ይህንን እንደ መዥገር ተጣብቆ የኢትዮጵያንና የሕዝቧን ደም እየመጠጠ ያለ ቆሻሻ ሥርዓት አስወግዶ ለሁላችንም የምትበጅ ኢትዮጵያን መገንባት ከሆነ፣ እንደየተደራጃችሁበት አስተሳሰብ በቅድሚያ አንድ ሁኑ፡፡ አጥጋቢ ባይሆንም በዚህ ረገድ አንዳንድ መልካም ጅምሮች ተስተውለዋል፡፡ ይህንን አጠናክራችሁ ግፉበት፡፡ መለያየታችሁና እርስ በርስ መናቆራችሁ የሕዝብን ስቃይ የወያኔን ዕድሜ ማራዘም መሆኑን የምታጡት አይመስለኝም፡፡ በሕዝብ ድምጽ አሸናፊ ብትሆኑ የምታገለግሉት በአመለካከት በአስተሳሰብ የእናንተ ፕሮግራም ራእይ ደጋፊ ያልሆነውን የኅብረተሰብ ክፍል ጭምር በመሆኑ ከጥላቻና ከመጠላለፍ ፖለቲካ ራሳችሁን አንጹ፡፡ ያለፈን ቁርሾ (በእውነት አንድን ጎሣ አነጣጥሮ የተፈጸመ ካለ) ማመንዠኽ ጋት ያህልም ስለማያራምደን ከስህተታችን የምንታረምበት፣ ዳግም እንዳይፈጸም እርም የምንልበት ይሁን፤ በቀደመ ዘመን/ታሪክ የተፈጸመ ግፍ በደል ካለ ይቅር ለእግዚአብሔር ለመባባል ሆደ ሰፊ እንሁን፤ ወገንተኝነታችሁ ለኢትዮጵያውያን በሙሉ ይሁን፡፡ እንወክላለን የምትሉት ሕዝብ በጎሣ፣ በሃይማኖት ወይም ወያኔ ባዘጋጀው የማለያያና ጥላቻን የማራቢያ ዘዴዎች እንዳይጋጭ፣ ኃይሉንም ረብ በሌለው ጉዳይ እንዳያባክን ተግታችሁና አጥብቃችሁ ልትሠሩ ይገባል፡፡ ወያኔን በጋራ አስወግደን ለምትመሠረተው ኢትዮጵያ ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ተወዳድራችሁ የሕዝብ ሥልጣን የምትይዙት ዓላማችሁን፣ ርእያችሁን፣ አጀንዳችሁን፣ ፕሮግራማችሁን በሚመርጥ የሕዝብ ዳኝነት ይሆናል፡፡

ሐ/ የሲቪክ ማኅበራት (በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምትገኙ)

ወያኔ በአፍራሽ ፖሊሲው ሕዝብን ለማለያየት አገርን ለማፍረስ ከዱር እስከ ቤተመንግሥት በእጅጉ ሠርቷል፡፡ በዚህ አፍራሽ ተልእኮውም በርካታ ንጹሐን ኢትዮጵያውን ያለ ፍርድ ሕይወታቸውን አጥተዋል፣ አካለ ጎደሎ ሆነዋል፣ በየወህኒ ቤቱ በእስር ይማቅቃሉ፣ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፣ ተሰድደዋል፣ የኢትዮጵያውያን ሀብት ንብረት ወድሟል፣ ተዘርፎአል፡፡ የእስካሁኑ ጥፋት አገርና

ሕዝብ ከሚሸከሙት በላይ ቢሆንም ወያኔ ተልእኮው ነውና ከእስካሁኑም ለከፋ ጥፋት እየተዘጋጀ ነው። በመሆኑም ተጨማሪ ጥፋት እንዳይከሠት፣ በዚህም ምክንያት የአንድ ኢትዮጵያዊ ሕይወት እንኳ እንዳይጠፋ የሲቪክ ማኅበራት ከፍተኛ ሚና ይኖራችኋል። ለዘመናት ተሳስቦ በችግርም በደስታም አብሮ ሲኖር የቆየው ኢትዮጵያው የአገዛዙ እኩል ተጠቂ መሆኑን በማስረዳት ጎሣና ሃይማኖቱን መሠረት አድርጎ እንዳይጋጭ ማስተማር፣ ማሳወቅ ይጠበቅባችኋል፤ ግጭቶችም ከቊጥጥር ውጭ ሳይሆኑ በምክር፣ በዕርቅ፣ በሽምግልና እንዲፈቱ ተሰሚነት ካላቸው ከአካባቢው ታዋቂ ሰዎችና ሽማግሌዎች ጋር መሥራት ይጠበቅባችኋል። መርጠው ፈቅደው ባላመጡት የጎሣ ማንነት እንዳይለያዩ፣ ያንን እውነታ (አኝዋክና መዠንገርነትን፣ በርታና ጉሙዝነትን፣ ሐረሪና ኢሮብነትን፣ ሽናሻና ሳሆነትን፣ አፋርና ሶማሌነትን፣ ሱርማና ሐመርነትን፣ ጉራጌና ትግሬነትን፣ ከምባታና ሀድይነትን፣ ጋሞና ወላይትነትን፣ ሲዳማና ከፋነትን፣ ወላይታና ኮንሶነትን፣ ኦሮሞና ‹ዐምሐራ›ነትን፣በጠቅላላው በኢትዮጵያችን ውስጥ የሚገኙ ጎሣዎችን) የሚሽር የሚያሳጣ ኃይል እንደሌለ ማስረዳት ይጠበቅባችኋል፤ ይልቁንም ሁላችንን የሚያስተባብሩ ትልልቆቹ የማንነት መገለጫዎች ማለትም የአንድ አገር ***ዜግነት*** እና ሰውነት (***የሰው ልጅነት***) ላይ እንዲያተኩሩ ተግቶ ማስተማር ያስፈልጋል። ወያኔ ተወግዶ ለሁላችን የምትሆን ኢትዮጵያን በምንመሠርትበት ሂደት የጎሣ ልዩነታችን መድመቂያችን መክበሪያችን ሆኖ፣ ትንሽ ትልቅ ሳይባል ተቋማዊ መሠረት ይዞ ባህሉን፣ ትውፊቱን፣ ታሪኩን፣ ቅርሱን፣ ማንነቱን እንዲያበለጽግ፣ በዚህም የቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን፣ ይህንንም ለተተኪ ትውልዶች ሥርዓት ባለው መንገድ ዘግቦ፣ ሰንዶ እንዲያቆይና እንዲያስተላልፍ ከሚመሠረተው ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትና መዋቅር በተጨማሪ የሲቪክ ማኅበራት ከፍተኛ እገዛ የማድረግ ኃላፊነትና አደራ አለባችሁ።

መ/ የብዙኃን መገናኛ (በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምትገኙ)

ያለንበት የመረጃ ዘመን ዘልማዳዊው ከሆነው የብዙኃን መገናኛ በተጨማሪ አምባገነኖች አዳፍነው የማያስቀሩት በርካት ዘመናዊ መረጃን የማስተላለፊያ/ ለሕዝብ እንዲደርስ ማድረጊያ መንገዶች አሉት። ውሸት እንደ ኮሶ የተጣባውን የወያኔን አፍራሽ መረጃዎች ከማምከን ጀምሮ ሞያዊ ኃላፊነትና ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ አገራዊና ተያያዥነት ያላቸው ዓለም አቀፋዊ መረጃዎች ለሕዝብ የማድረስ ግዴታ አለባችሁ። ጦማርያን ሆናችሁ ሌሎች የማኅበራዊ ብዘኃን መገናኛ ተጠቃሚዎች እርስ በርስ ከመዘላለፍና ከመነቃቀፍ ወጥታችሁ (ወያኔና የአገዛዙ ተጠቃሚዎች ካልሆኑ በስተቀር ሌሎቻችን ለእንቶ ፈንቶ የምናባክነው ጊዜና ኃይል የለንምና) ኢትዮጵያዊ ጨውነት በተሞላበት፣ እውቀትንና ሞያን መሠረት ባደረገ እንዲሁም በለዘበ ቋንቋ ለሕዝብና ለአገር የሚጠቅሙ ሃሳቦችን፣ አለመካከቶችን፣አስተያየቶችን፣ ትችቶችን ብትለዋወጡ መልካም ይመስለኛል። ነፃነት ልቅነት/ስድነት አይደለም። ገደብ ያለው፣ በኃላፊነት የሚጠቀሙበት

የባለአእምሮ ወይም አስተዋዮች የማሰብ፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ እነዚህንም በሥራ የመተርጐም ምርጫ ነው።

ሠ/ የኢትዮጵያ ሕዝብ (በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኘው)

ሽብርተኛው የወያኔ አገዛዝ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የኢትዮጵያን ሕዝብ እየጨፈጨፈ ይገኛል። ይህ የሕይወት መሥዋዕትነት ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርና በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል ሕዝባዊ እምቢተኝነቱ እንዲቀጣጠል ከተፈለገ ሕዝቡ ከወያኔ ሌላ ጠላት እንደሌለው ጠንቅቆ መረዳት ይኖርበታል። የወያኔ ራዲዮና ቴሌቪዥን በሚያሰራጨው ሐሰትና ተረት ሳይታለል፣ ባሰማራቸውም ሆድ አደር ካድሬዎች ከንቱ ዲስኩር ሳይደናገር በቅድሚያ ከየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የመጣውን ወገኑን ለዘመናት አብሮ የኖረም ይሁን በቅርብ የመጣ ወገኑ መሆኑን በማመን ምንም ዓይነት ጥቃት ላለማድረስ እያንዳንዱ ዜጋ ከራሱ ጋር ቃል ኪዳን ሊገባ ይገባዋል። ምክንያቱም ኢትዮጵያ አገራችን ለሁላችን የምትበቃ የጋራ ርስታችን ናትና። ዛሬ ወያኔ ጎልውናዋን ለሚፈታተናት አገራችን በአራቱም ማዕዘናት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን አባቶችና እናቶቻችን ውድ ሕይወታቸውን ከፍለው ባንድነት በነፃነት ያቆዩልን የጋራ ቤታችን ናትና። እናቱ ቤት ሊኖር የፈለገን ሰው ማንም እንደ ባዕድ እንደ ጣላት ሊቆጥረው አይችልምና። ይልቁንስ የእኛ ኢትዮጵያውያን ደገኛ ባህላችን እንኳን ወገናችንን ሰላማዊ እስከሆኑ ድረስ ባዕዳን እንግዶችን ቤት ለእንግዳ ብለን አንጥፈን ጎዝጉዘን የምንቀበል አይደለንም? በዚህ ረገድ ለእውነት የቆማችሁ የእምነት አባቶች እንዲሁም የአገር ሽማግሌዎች ካላችሁ የተጣላውን አስታርቁ፤ የበደለው እንዲክሥ አድርጉ፤አጥፊውን ምከሩ፣ ገሥጹ፤ ፍቅርን፣ አንድነትንና ወንድማማችነትን ስበኩ። ተማሪዎችም ይህ ጽሑፍ አገር ለወገን ይጠቅማል ብላችሁ ካሰባችሁ መልእክቱን ለቤተሰቦቻችሁ እንድታስተላልፉ በኢትዮጵያ አምላክ ስም እማፀናችኋለሁ።

በመጨረሻም የኛ ንስሓ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ በቀደመው ዘመንም ሆነ በቅርቡ ሕዝባችንና አገራችን ላይ ላደረስነው በደል ተጸጽተን ይቅር ለእግዚአብሔር መባባል ነው፤ ዕርፍ ተይዞ ወደ ኋላ አይታረስምና ሁላችንን በእኩልነት የምታስተናግድ ኢትዮጵያን ለመገንባት በጎ አሳቡ፣ ውይይቱና ሥራው ከአሁን መጀመር አለበት፤ ለዚህ ክቡርና ታላቅ ዓላማ ማን ቤዛ/ታዳጊ ይሁነን? ያለምንም ጥርጥር ሁላችን ኢትዮጵያውያን፤ በግንባር ቀደምትነት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ከባርነት ወደ ነፃነት፣ ከነሣር ወደ ክብር፣ ከድህነት ወደ ብልጽግና፣ ከዘራፊዎችና አምባገነን ሥርዓት እኩልነት፣ የሕግ የበላይነትና ፈቃደ ሕዝብ ወደ ሰፈነበት ሥርዓት ለማሸጋገር ዝግጁነቱ ያላችሁ የሕዝብ መሪዎች።

ይኄይስ እውነቱ